# እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!

<u>በቤተ ክርቲያን የተዘጋጀ ታላቅ ሪትሪት</u>

ቀን፡ **7/4 - 7/6/2019**
**አድራሻ፡** W2511 WI-23, Green Lake, WI 54941 (Takes about 3 hours to 3:30 hours)
**Phone** = (920) 294-3323 Booking ID number= 14589
For making reservation please call during the below hours
**Sunday - Thursday 8:30-4:30**
**Friday - Saturday 24 hours**
**When reserving rooms please provide the date, the name Yemsrach how many people will be in the room.**

### የአርብ ፕሮግራም

በአርብ ፕሮግራም እግዚአብሔር ግሩም የጸሎትና የትምህርት ጊዜ እየሰጠን ነው። በዚህ የጸሎት ፕሮግራም ላይ በመገኘት በጸሎትና ቃሉን በመማር እንድንተጋ ቤተ ክርስቲያን ታሳስባለች። እንዲጸለይላችሁ የምትፈልጉ ወገኖችም መሪዎችን ማነጋገር ትችላላችሁ። ጌታ ይባርካችሁ።

"ወደ ውጭም አውጥቶ፡- ጌቶች ሆይ፥ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? አላቸው።
እነርሱም፡- በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ አሉት።" (ሐዋ. 16፡ 30-31)



- ⇒ የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ በምጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?
- ⇒ ማገልገል ይፈልጋሉ?
- ⇒ Yeec.org App ጭነዋል?
- ⇒ http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?

**ሽማግሌዎችን ለማግኘት፡-**
773-886-0818 (ወ/ም ሲሳይ)
773-507-0147 (ወ/ም ጸደቀ)
630-677-0293 (ዶ/ር ተረፈ)
773-910-0486 (እ/ት ሰናይት)
773-556-5345 (ወ/ም ረድኤቱ)

<u>መደበኛ ፕሮግራሞች</u>
እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.

| የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን | | Chicago Yemsrach Evangelical Church |
|---|---|---|

"እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ" ሉቃስ 2፡10




"እግዚአብሔር እረኛዬ ነው፥ የሚያሳጣኝም የለም።"
(መዝ. 23፡1)

Chicago Yemsrach Evangelical Church
4455 N. Seeley Avenue
Chicago, IL 60625

መደበኛ ፕሮግራሞች
እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.

**April 14, 2019** **ሚያዚያ 6፣ 2011 ዓ.ም.**

## የእለቱ አገልግሎት መርሃ-ግብር

| | |
|---|---|
| ጸሎት ................. | ወንድም ብርሃኑ አንበሴ |
| አምልኮ....................... | ወንድም ጌታያውቃልና እህት ብሩክታይት/የአምልኮ ቡድን |
| ፕሮግራም መሪ .......... | ወንድም ሲሳይ መሸሻ |
| ቃል ............. | ወንድም ጌታያውቃል ግርማይ |
| ማጠቃለያ ................. | ፕሮግራም መሪ |

### የሳምንቱ ጥቅስ

"በክርስቶስ በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ።"

(ኤፌ. 1፡3)

| የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች | | |
|---|---|---|
| መሪ | ቀን | አድራሻ |
| ወ/ም አያሌው አስፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 7526 N. Ridge Blvd., Unit #3W, Chicago IL 60645 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ሃሙስ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ዮናስ ባህሩ | ማክሰኞ | 5523 N. Kenmore Ave., Chicago, IL 60640 |
| | | |

## መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ካሳ

### ተባርከናል!

ምድራዊ ሕይወት በረከትን ለመያዝ የሚደረግ ሩጫ የበዛበት ነው። ሰዎች የባለጠግነትን በረከት ለማግኘት ይጥራሉ፤ ዝናንም ለማግኘትም ብዙ መንገድ ይሄዳሉ፤ የስልጣንምም እርከን ለመውጣት ብርቱ ፍልሚያ ያደርጋሉ። በብዙ ሃይማኖቶችም ሰዎች የጽድቅን በረከት ያገኙ ዘንድ ስረአቶችን ለመፈጸም ይታገላሉ። ሰው በራሱ በረከትን ለማግኘት የሚያደርገው መውተርተር የበረከት ጫፍ ላይ አድርሶ የሚሳርፍ አይደለም። ይልቁንም በብርቱ ጥረትና ግረት የያዙት ነገር ሲጨብጡት ምንም እየሆነባቸው ሌላ ከፍ ያለ የበረከት መሰላል ላይ ለመውጣት ያልማሉ። ፍላጎታቸውም እንደ የሚሸሽ ኢላማ ከፊታቸው አያመለጠ ይቀድማቸዋል። አንድ ጊዜ እውቁ ቱጃር ጆን ዲ ሮክፌለር ለአንድ ሰው ምን ያህል ገንዘብ ይበቃዋል ተብለው ሲጠየቁ "ባለህ ላይ ጥቂት ሲጨማር" በማለት መመለሳቸው ይነገራል። ምድራዊው ሰው ሁልጊዜ ባለው ላይ ጥቂት መጨመር ይፈልጋል። የፈለገውን "ጥቂት" ሲጨምር ደግሞ ሌላ "ጥቂት" መጨመርን ይሻል። እንዲህ እያለ ሰው የማይሞላ የበረከት ቋት ሊምላ ሲዳክር ሕይወቱን ይፈጃል።

ክርስትና ግን የሚጀምረው "ትባረካለህ" ብሎ ሳይሆን "ተባርከሃል" ብሎ ነው። ክርስትና በረከትን የመፈለግ ሩጫ ሳይሆን እንደተባረከን ተረድተን፤ የበረከታችንን ጥልቀትና ብዛት እየተረዳን በምድር እግዚአብሔር እንድፈጽመው የሰጠንን ስራ እየሰራን መኖር ነው። በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር እስራኤልን "አንተ ብሩክ ነህ፣ እግዚአብሔር ያዳነው ሕዝብ እንዳንተ ያለ ማን አለ?" (ዘዳ. 33፡29 ኢ.መ.ት.) ይለዋል። የእስራኤል በረከት የእርሱ ጥረት ውጤት ሳይሆን በእግዚአብሔር የመመረጡ ጉዳይ ነው። የሕዝቡ በረከት እርሱ እራሱ እንጂ በእርሱ ያገኙት የምድር ሲሳይ አልነበረም። ስለዚህም "መኖሪያህ የዘላለም አምላክ ነው፤ የዘላለምም ክንዶች ከአንተ በታች ናቸው" ይለዋል። (ቁ. 27) አዲስ ኪዳንም የሚያስተምረን እግዚአብሔር "በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ" በሰማያዊ ስፍራ እንደ ባረከን ነው። አሁን ተባርከናል! ከዚህ በኋላ የሚያስደንቀን ነገር ቢኖር የበረከቱ መገለጥ ነው። የተባረከንበት የበረከት ጥልቀት አሁን ካለን የመረዳት አቅም የሚያልፍ ነው። ነገር ግን አንድ ነገር እናውቃለን። እኛ በረከትን ለማግኘት የምንውተረተር አይደለንም። በክርስቶስ ተባርከናል። የምድር ሁኔታችን ምንም ይሆን ምን የተባረከን ሰዎች ነን። በረከታችን እሩሱ እራሱ ነው። ለዚህም ነው ቃሉ እርሱን ማለትም መንግስቱንና ጽድቁን እንድንሻ የሚመከረን። በሰማይ በረከት የባረከን አምላክ በሚያስፈልገን የምድር በረከት አያጎድለንም። ምድራዊው ነገር ቢጎድልም እንኳ እንባቆም እንድዘመረው መንፈሳዊ በረከታችንን እያየን በመስጋና ሙላት ውስጥ እንዳንገባ አይከለክለንም።

ወገኖቼ፡- የተባረከ ሕዝብ አመስጋኝ ነው። ለዚህም ነው ሐዋሪያው ጳውሎስ ምንም እንኳ ይህንን መልዕክት ሲጽፍልን በእስር ላይ ቢሆንም "የባረከን ይባረክ" ብሎ ለምስጋና የሚጋብዘን። እግዚአብሔር አምላኩ የሆነለት ሕዝብ ብሩክ ነው። የበረከት ቁንጮ ላይ ደርሷል። ስለዚህም የበረከቱን አምላክ በምንም ሁኔታ ውስጥ ያከፍራል። እግዚአብሔር በረከቱ ነው ስንል ስለ "አሳው" አይገደንም፤ ካስፈለገ መረባችን እስቂቀደድ ይሞላዋል። ንጉሱ ዳዊት እንደዘመረው እግዚአብሔር እረኛችን ነው። የሚያሳጣን የለም። አሜን!